# እርሱን ስሙት

የዓለምን ጥበብ አምላክ ስለናቀው
ወደምድር መጣ አዳምን ሊያድነው።
ደካማውን ሥጋ ለብሶ ተዋህዶ
በመስቀል ሞኝነት ጥበብን አዋርዶ።

    የሰው ልጅ ግን ልቡ እጅግ ደንድኖበት
    የአምላክ ሥጋ መልበስ አልታይህ ብሎት
    ይከሰው ጀመረ የሰንበቱን ጌታ
    ትምህርቱን ሳይሰማ ሳያስተውለውም የፈውሱን ውለታ።

ትዕዛዝነው የመጣ ከላይ ከፀባኦት
ደመና ተጭኖ የተላከ መልዕክት
በጣም የምወደው አንድያ ልጄ ነው !
እርሱን እንድትሰሙት ልኬዋለሁ ይኼው
ብሎ መሰከረ አብ ደጉ አባት
በታቦር ተራራ ከሐዋርያቱ ፊት።

    ከሙታን መካከል ሙሴንም ጋበዘው
    ተመኝቷልና የአምላኩን ፊት ሊያየው።
    የትንቢቱን ፍሬ ለማየት ማዳኑን
    ኤልያስም ተገኝቷል ከብሔረ ህያዋን።

እኛ ግን አምነናል የእርሱን አምላክነት
ድምጹንም ሰምተናል አብ ሲመሰክርለት።
አይተናል ሲቀየር ልብሱ ሲያንጸባርቅ
ንፃቱ የሚያስገርም እጅግ የሚያስደንቅ።
አብረን እዚያው ነበርን በቅዱሱ ተራራ
ከጴጥሮስ ከያዕቆብ ከዮሐንስ ጋራ ።

    ለአህዛብ እንዲደርስ በዓለም ተሰብኳል
    አሁንም እንስማው የክርስቶስን ቃል ።
    መዳን በእርሱ ነው ቃሉን በመስማት
    መሆን የሚቻለው የአምላክ ልጅነት
    መግቢያ በር እርሱ ነው ለዘላለም ህይወት
    ሰምተን እንተግብረው ቃሉንም በእምነት።

ዘማሪ ክንፈ ሚካኤል